
# የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት
# (ሐዲድ)
## የፖለቲካ ፕሮግራም



ጥቅምት 2000

# I. መግቢያ

የኢትዮጵያ ብሔሮች ብሔረሠቦችና ሕዝቦች ከአንድ ምዕተአመት በላይ የነበሩ ገገር መደቦች ይከተሉት የነበረው ስር የሠደደ ጭቆና፣ ብዝበዛ፣ግድያና ስደት ምክንያት ታሪካቸው ቋንቋቸውና ባህላቸውን እንዳይከተሉና እንዳያሳድጉ የአፈና ፓሊሲያቸውን በመጫን አገሪቱን ወደ ባሰ ድህነትና ህዝቦቿም ወደ መበታተን ማምራቱ ይታወቃል ::

የኢትዮጵያ ህዝብ ብሔራዊ ጭቆና በተጨማሪም የዜግነት መብታቸውን በመንፈግ በሰላም ሰርቶ የመኖር የኢኮኖሚያዊ መብታቸውን በማጣታቸው በነበረው አስከፊ ስርአት ለሞት ለስደት ለረሐብና ለዕርዛት ተዳርገዋል::

ሆኖም ይህን አስከፊ የግፍ ስርአት ህዝቦች አሜን ብሎ የተቀበሰበት ሁኔታ አልነበረም በአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘኖች የህዝብ ተቃውሞና አመጽ እየተስስፋ በመሄድ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር ( ኢህአዴግ) ከጭቁን ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጋር ባደረገው መራር ትግል ደርግ ከስልጣን ተወግዶ በምትኩም ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብታቸው ህገመንግስታዊ ዋስትና አግኝተው ራሱን በራሱ በማስተዳደር በአገሩ ጉዳይ ተሳታፊና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ስርአት ተፈጥሯል::

በኢትዮጵያ ከሚኖሩ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አንዱ የሐረሪ ህዝብም የራሱ የሆነ ገናና ታሪክ የነበረውና ራሱን በራሱ ያስተዳድር የነበረ ህዝብ ሲሆን በምስራቅ ኢትዮጵያ ክፍል ዋና ከተማውን ሐረር በማድረግ በጥንታዊ ስልጣኔዋ የምትታወቀው ሐረር ህዝቧ ራሱን በራሱ ሲያስተዳድር የኖረ ህዝብ ሲሆን ቋንቋውን ታሪኩን ጠብቆ የቆየና 72 አሚሮች የነበሩትና የራሱ የሆነ የመገበያያ ገንዘብ የነበረው በምስራቅ አፍሪካ ለረዥም ጊዜ የንግድ፣የእስልምና ሀይማኖትና የመስተዳድር ማዕከል ነበረች ::

ግብርና የህዝቡ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሰረት ሲሆን ከዚህም ጎን ለጎን በንግድና በተወሰነ መልኩም በጎጆ ኢንዱስትሪዎች ይተዳደር እነደነበረ የታሪክ መረጃዎች ያስረዳሉ ::

ሐረር ለረዥም ጊዜ ራሱን በራሱ ሲያስተዳድር የራሱ የሆነ አስተዳደራዊ መዋቅር ፍ/ቤት ሰራዊት የነበረው ሲሆን ከአካባቢው ህዝቦች ጋር በባህላዊ ፌዴራሊዝም (Traditional Federalism ) በማቋቋም ብሔርብሔረሰቦች ጋር በመተባበርና በመከባበር ለረዥም ዘመናት አብሮ ይኖር የነበረ ህዝብ ነው ::የሐረሪ ህዝብ እ.አ.አ 1887 በጨልቆ ጦርነት የራሱን በራሱ

የማስተዳደር መብት በወራሪው የሚኒሊክ ጦር ተነጥቆ ለጭቆና ቀንበር ተዳርጓል :: በጦርነቱም ከ 700 በላይ ሙሽሮችን ጨምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የሐረሪ አርበኞች ተሰውቷል:: በዚሁ ጦርነት ወራሪው የአፄሚኒሊክ ጦርም ሐረርን በሀይል ተቆጣጥሯት የህዝብ ንብረት ተዘረፈ ህዝቡም ለሞት ለስደትና ለእስራት በመዳረጉ የህዝቡ ብሔራዊ መብት በመረገጥ አስከፊ ጭቆና ውስጥ ጥለውታል::

የሐረሪ ህዝብ ሉአላዊነታቸው ከተነጠቀበት ከ1887 ጀምሮ እስከ ነፍጠኛው የደርግ ስርአት ህዝብ በአገሩ እንደ ሁለተኛ ዜጋ በመቆጠሩ ጭቆናውን ለመቀልበስና መብታቸውን ለማስከበር የተለየ ትግሎች አካሂዷል:: የአሚር አብዱላሂ ጦር በጨለንቆ ጦርነት ሽንፈት ከደረሰበት በኃላ ከወራሪው አፄ ሚኒሊክ ጦር ጋር በመደራደር በሐረሪዎች የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዳይገባ በሐረሪዎች ሃይማኖት ጣልቃ እንደ ማይገባና ተፅእኖ እንደማያደርግ እና የውጭ ወራሪ ሀይል ከመጣ መረጃ መስጠትና በየአመቱ 40 ሺ. ማርትሬዛ ግብር በመክፈል ተስማምተው ወራሪው ጦር ውሉን በመጣሱ በርካታ ሀረሪዎች ለሞትና ወደ ጎረቤት ሀገሮች ለመሰደድ ተገደው ለከፋ ስቃይና ጭቆና ተዳረጉ አስከፊው የነፍጠኛ ስርአት ጭቆና የሐረሪ ሕዝብ ከፍተኛ የፓለቲካ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚ መብት ጭቆና ቀንበር ውስጥ በመዳረጉ የተለያዩ የመብት ትግሎችን በህቡዕና በይፋ መታገል ጀመሩ በዚህ የህዝብ ንቅናቄና ትግል ከፍተኛ የህይወትና የንብረት መስዋዕትነት በመክፈል ተቋውሟቸውን ሲገልጹ በመጨረሻም ኢህአዴግ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በመሆን ባደረገው የትጥቅ ትግል የደርግ መንግስት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተገርስሷል ::

በምትኩም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በማስከበር የዜጎች ህገመንግስታዊ መብት ተከብሮ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት በመጠቀም ወደ አዲስ ዲሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ግንባታ ገብ ጀምሯል ::

የኢፊድሪ ህገመንግስት በተደነገገው መሰረት የሐረሪ ህዝብ ክልል አንድ ክልል በመሆኑ የሀረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብቱን ለማስከበር የራሱ ም/ቤት ተቋቁሞ የክልል ሞ/ቤት አስፈፃሚ አካል ህግ ተርጓሚ አካል በማቋቋም በስፋት አስራስድስት አመታት የክልሉን ህዝብ የሐረሪ ብሔራዊ ሊግና የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት በጋራ ክልሉን በመምራት ላይ ይገኛሉ::

ባለፉት ሶስት የምርጫ ዘመናት ሐብሊ የሐረሪን ሕዝብ በመወከል ክልሉን የመምራትና የማስተዳደር ሀላፊነት የወሰደ ቢሆንም እንደ ገዥ እና መሪ ፓርቲ መላውን የሀረሪ ህዝብ በማስተባበርና በማነቃነቅ የህዝቡን የፓለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መብቶች በማስከበር ክልሉን ለማልማትና የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ አልተቻለም:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ድርጅቱ የጠራ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊና ልማታዊ አስተሳሰብና ተግባር የታነፀ አደረጃጀትና

አሰራር ባለመኖሩና ምልአተ ህዝቡን ያሳሳተፈና ተጠቃሚ ያላደረገ በመሆኑ ድርጅቱን ከወደቀበት የጥገኝነት አረንቋ ለማውጣት የተደረጉ ጥረቶች ሊሳኩ ባለመቻላቸው ህዝቡን የመብት ጥያቄ በአግባቡ አደራጅቶ በልማታዊና አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መንገድ አደራጅቶና አስተባብሮ አንድ ጠንካራ ፖለቲካ ፓርቲ በመመስረት በክልሉና ከክልሉ ውጪ እንዲሁም በውጭ የሚኖሩ ሐረሪዎችን በማስተባበር ብሔራዊ መብታቸው በማስከበር ነዋሪዎችን ዲሞክራሲያዊ መብታቸውን በማክበር በልማት ተሳታፊ እንዲሆኑ ከ ኦሮሞ ህዝብ ጋር ያለው ልዩ ታሪካዊ አጋርነት ተጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረግ በክልሉ የሰላም የልማትና የመልካም አስተዳደር እመርታ ማስመዝገብ የህዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄ በመሆኑ የሐረሪ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት (ሐዲድ) መመስረት አስፈልጓል::

## II ዓላማ

የሐረሪን ሕዝብ በአብዮታዊ ዲምክራሲያዊና ልማታዊ አስተሳሰብ በአንድነት በማሰባሰብ ጠንካራ መሪ ፓርቲ መመስረት

1 የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብት ማስከበርና በክልሉ የስልጣን ባለቤት እንዲሆን መታገል

2 በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎችና በመላው አለም የተበታተኑ ሐረሪዎችን በማሰባሰብ እና በማደራጀት በክልሉ ፓለቲካዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ

3 በኢፌድሪ ህገመንግስት የተደነገጉ የግልና የቡድን መብቶች እንዲከበርና የህዝቦች እኩልነትና ተጠቃሚነት እና የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ መታገል ::

4 ስር የሰደደውን ድህነት ደረጃ በደረጃ በመቅረፍና ፈጣን ልማትን በማረጋገጥ በክልሉ መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን መታገል

5 የነፃ ገበያ ስርአት እንዲጎለብትና የልማት ፓሊሲ ስትራቴጂዎችን በአግባቡ በመተግበር በክልሉ የተሻለ የልማት ውጤት ለማስመዝገብ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ፣ የግል ባለሀብቱንና መላውን ሕብረተሰብ በአግባቡ አቀናጅቶ መምራት

6 ልማታዊና አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ የፓለቲካ ስርአት እንዲሰፍን መታገል

7 በክልሉ የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች መብታቸው ተከብሮ በሰላም እና በመቻቻል ተባብረው በጋራ ክልላቸውን የሚያለሙበት የሚሳተፉበትና ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሁኔታ ማመቻቸት

8 የዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ በማጠናከር ሕዝቡ የሚሳተፍባቸውን የተለያዩ የሞያና የሲቪክ ማህበራትን በማደራጀት ዲሞክራሲያዊ ተቋሚትን ማስፋፋት

9 ህብረተሰቡ የመልካም አስተዳደር ተጠቃሚ እንዲሆን ዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በማቋቋም የአገልግሎት አሰጣጥ ስርአት በአግባቡ እንዲሰጥ ማድረግ ::

# የፓለቲካ ፕሮግራም

1 የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ መብት ተጠብቆ በክልሉ ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል መብታቸው እንዲከበር መታገል

2 ባለፉት ገገር መደቦች ሐረሪዎች ከትውልድ ቀየአቸው በመፈናቀል በመላው አለም የተበታተኑትን ወደ ክልላቸው ተመልሰው ክልሉንና ሀገራቱን እንዲያለሙና እንዲሳተፉ በማድረግ የህዝቡ ፍልስት እንዲቀንስ ማድረግ ::

3 የሐረሪ ህዝብ ቋንቋውን ታሪኩን እና ባህሉን እንዲያደብርና ቅርሱን በመንከባከብና በመጠበቅ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፍ ለማድረግና የሀረሪ ቋንቋ የክልሉ የስራ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ

4 የህዝቦች ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩና ሕዝቦች ሀሳባቸውን ያለተፅኖ መግለፅና ማራመድ እንዲችሉ መታገል

5 ልማታዊና አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ልዕልና እንዲያገኝ ለህብረተሰቡ ተከታታይነት ያለው የፓለቲካ አቅም ግንባታ በመስጠት ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ ፖለቲካ ኢኮኖሚ እንዲመጣ መታገል

6 አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ መስመር ከሚከተሉት ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት በማጠናከር ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በጋራ ጉዳይ ላይ በመወያየት በጋራ አብሮ መስራት::

7 የህዝቡን የስልጣን ባለቤትነት በማረጋገጥ ህዝቡ ቀጥተኛ ተሳታፊ በማድረግ የላይኛው የስልጣን እርከን ወደ ታችኛው እንዲዘረጋ ማድረግ

8 በህዝቦች እኩልነትና በመፈቃቀድ የተመሰረተውን የኢትዮጵያን ህዝብ አንድነት በማጠናከርና የህግ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ

9 የጥገኝነት የፓለቲካ ኢኮኖሚን ለመናድ ጥገኞችን መሸከም የማይችል የፓለቲካ ኢኮኖሚ እንዲመጣ ትግል ማድረግ ::

# የኢኮኖሚ ፕሮግራም

1. የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርአት በህብተረሰብ ተሳትፎ ህዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ
2. የኢንዱስትሪና የከተማልማት ፓሊሲና ስትራቴጂ በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ
3. የክልሉ የኢንቨስትመት ፓሊሲ በመተግበር በክልሉ እምቅ የኢኮኖሚ ሀብቶች በማጥናት የግል ባለሀብቱ በሰፋት እንዲሳተፉና ክልሉን እንዲለማ ማመቻቸት
4. የክልሉ ባህለዊ ቅርሶችን በመጠበቅና በመጠገን የክልሉ የቱሪዝም ፓሊሲ በመንደፍ የክልሉን ልማት ማሳደግ
5. የዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያለውን የህብረተሰብ ክፍል ለማሳደግ የጥቃቅንና አነስተኛ ንግድ በማስፋፋት የብድር ተቋማትና የህብረት ስራ ማህበራትን በማስፋፋት ባህላዊ እደጥበባት ውጤቶችን እንዲስፋፋ ማድረግ
6. የተፈጥሮ ማዕድናት እምቅ ሀብት በዝርዝር በማጥናት ለክልሉ ልማት በአግባቡ እንዲውል ማድረግ
7. የክልሉን ልማት ለማፋጠን የመሰረተልማት አቅርቦትን በማሻሻል የከተማ መልካም አስተዳደር ፕሮግራምና የተቀናጀ የከተማ ልማት ፕሮግራምን በስራ ላይ ማዋል
8. የመንግስት የታክስ መሰረትን በማስፋት ህጋዊ ንግድ እንቅስቃሴን በማበረታት ህገወጥ ንግድና ኮንትሮባንድን መከላከል ::

# ማህበራዊ ፕርግራም

1. የሐረሪ ህዝብን ባህልና ታሪክ በአግባቡ እንዲጠበቅና እንዲዳበር ማድረግ::
2. የሐረሪ ሕዝብ በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመጀመሪ ደረጃ ትምህርት እንዲሰጥና ሐረሪኛ በሁሉም ት/ቤቶች እንዲማሩ ማድረግ::
3. የአቅም ግንባታና የትምህርት ፓሊሲን በአግባቡ በስራ ላይ ማዋል
4. የጤና አጠባበቅ ፓሊሲን በአግባቡ በስራ ላይ ማዋል
5. የማህበራዊ ጠንቆችን በመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል ፓሊሲና ፕሮግራም መንደፍ
6. የወጣቶችና የሴቶች የስፓርት ፓሊሲን በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ አገናዝቦ በስራ ላይ ማዋል::